# ምዕራፍ አሥራ አንድ

# ዕውቀትን መሻት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፣** ***ይህንን ምዕራፍ ተምረህ/ ተምረሽ ስታጠናቅቂ/ ስታጠናቅቅ፤***

- ዕውቀት ስልማት፣ ስምርምርና ስፈጠራ መሠረት መሆኑን ትገነዘባለህ/ትገነዘቢያለሽ።
- የመረጃን አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ትረዳለህ/ ትረጃለሽ፡፡
- የመረጃ ምንጮችን፣ የመረጃ አያያዝንና የአጠቃቀም ዘዴዎችን ታውቃለህ/ቂያለሽ፡፡

## 11.1 ሣይንሳዊ ጠቀሜታ

### 11.1.1 የሣይንሳዊ ዕውቀቶች ጠቀሜታ



*ሥዕል 11.1 ምርምር በላቦራቶሪ*



*ሥዕል 11.2 የአርኪኦሎጂ ምርምር*

- ከሥዕሎቹ ምን ትረዳላችሁ?
- በቤተሙከራ ውስጥ የሚታየው ሥዕል ስለ ሳይንሳዊ አመለካከት ምን ያመለክታል?



*ሥዕል 11.3 መምህርት በክፍል ውስጥ*

**የሌሊት ወፍ፤**

በድሮ ጊዜ የሌሊት ወፍ በምትኖርበት አካባቢ አስጨናቂ ረሐብ ገባ፡፡ በአካባቢው የሚኖሩት አእዋፋትና ሌሎችም እንስሳት በረሐቡ ክፉኛ ተጠቁ፡፡ ረሐቡን ለመቋቋም የሌላቸው ካላቸው እየተበደሩ ይበሉ ጀመር፡፡ ከተበዳሪዎቹም አንዷ የሌሊት ወፍ ነበረች፣ ከተለያዩ ወፎች ብዙ ተበ ድራ ነበር፡፡ ክፉው ቀን ካለፈ በኋላ ሌሎቹ ወፎች ሁሉ ያለባቸውን ብድር መክፈል ሲችሉ የሌሊት ወፍ ግን ተበድራ የበላችውን መመለስ አቃታት፡፡



*ሥዕል 11.4 የሌሊት ወፍ*

ጨረሻም አበዳሪዎቿ ሁሉ አጥብቀው ይፈልጓት ጀመር:: እሷ ግን በመደበቅ ማምለጥን መረጠች:: ከዚህም የተነሳ እንደሌሎቹ ወፎች ቀን መብረሯን አቁማ ምግቧን ለማግኘት ሌሊት መብረር ግዴታዋ ሆነ፣ በዚህም የሌሊት ወፍ ተባለች::

*(ከቃላዊ ትረካ የተገኘ)*



*ሥዕል 11.5 ግመል*

## መልመጃ 1

### *የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ::*

?

1. "የሌሊት ወፍ" የሚለው ጽሑፍ በተጨባጭ ዕውነታ ላይ ተመሥርቶ የቀረበ ነው? ለምን?
2. ስጥያቄ ቁጥር አንድ ከሰጣችሁት መልስ በመነሳት ሳይንሳዊ ስላስሆነ አመለካከት ምን ተረዳችሁ?

### ግመል፤

ግመል ከፈረስ ይበልጣል:: በአካሉም ከሌሎች እንስሳት ግዙፍ ነው:: ሲጫንና ሲራገፍ ይንበረከካል:: ሲቆምም ባሰበ ጊዜ መጀመሪያ የኋላ እግሮቹን ያነሳል:: ሰው ተቀምጦበትም ግመሉ ሲነሳ ሰውየው አጥብቆ ካልያዘው ወደግመሉ ራስ ሊወረወርና ሊወድቅ ይችላል:: ግመል ጠንካራ ከመሆኑ የተነሳ ከባድ ዕቃ ለመሸከም ይችላል::

ግመል በሰሜን ሕንድ፣ በአረብ አገሮችና፣ በአፍሪካ በረሃማ አካባቢዎችም ጭምር ከፍተኛ ጥቅም አለው:: ውሃ ሳይጠጣ ብዙ መጓዝና ከአራት እስከ አምስት ቀናት መቆየት ይችላል:: የተወሰኑት የግመል ዝርያዎች በጀርባቸው ላይ አንድ፣ ሌሎች ደግሞ ሁለት ሻኛ አላቸው:: ሻኛው የስባ ነው:: ግመሉ ሳይበላ ለብዙ ቀናት በሚቆዩበት ጊዜ ሻኛው እየሟሸሸ እንደ ምግብ ያገለግለዋል::

የግመል እግሮች ትልልቅ፣ ሰፊና ለስላሳ ሆነው በወፍራም ቆዳ የተያያዙ ናቸው:: በበረሃ ውስጥ በሞቀ አሸዋ ላይ በቀላሉ እንዲራመድ ይረዱታል:: ግመል ሲራመድ በቀስታ ነውና ባጠገባችን ቢያልፍ አንሰማውም::

የግመል አፍንጫ ጠባብ ስንጥቅ ኖሮት በቀላሉ መዘጋትና መከፈት የሚችል ነው:: አሸዋ በነፋስ ሲቦን ግመሉ ይተኛና አፍንጫውን ዘግቶ ራሱን በአሸዋው ውስጥ ይቀብራል:: አፍንጫው ከርቀት የውሃ ሽታ ለመሳብ ይረዳዋል:: አንዳንዴ መንገድን በማሳበር በአቋራጭ ይሄድና ውሃው ካለበት ሥፍራ ይደርሳል:: በዚህ ሁኔታ መንገደኞች በቀላሉ ውሃ ካለበት እንዲደርሱ ያግዛቸዋል::

*(ከበደ ሚካኤል፣ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

## መልመጃ 2

### *በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::*

?

1. "ግመል" የሚለውን ጽሑፍ ያቀረበልን ጸሐፊ የሚነግረንን ሐሳብ እውነተኛነት ማረጋገጥ ይቻላል? እንዴት?
2. እስካሁን ካስተዋላችሁት ሁኔታ ተነስታችሁ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲባል ምን ገባችሁ? በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ:: የደረሳችሁበትን ማጠቃለያም በክፍል ውስጥ አቅርቡት::

ዕውቀትን መሻት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ባሕርይ ነው፡፡ ዕውቀት ሲፈለግ ታዲያ በሳይንሳዊ አስተ ሳሰብ ላይ የመመሥረት ሂደት አለው፡፡ ሳይን ሳዊ አስተሳሰብ፣ ስለራሳችን ስለአካባቢያችንና ስለዓለም የምንመሠርተው ተጨባጭ ግንዛቤና ዕውቀት ነው፡፡

ይህም አስተሳሰብ በተለያዩ መንገዶች በምናገኛ ቸው መረጃዎች ስፋትና ጥበት እዲሁም ቅለትና ጥልቀት ይወሰናል፡፡ ይህም ሲባል ከዕድሜያ ችን፣ ከልምዳችንና ከትምህርት ደረጃችን በምናገ ኘው መረጃ ላይ ተመሥርቶ የሚያድግ የሕሊና ሀብት ይሆናል ማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋር የሳ ይንሳዊ አስተሳሰባችን ጥንካሬ ባለን ትክክለኛ መረጃና ተግባራዊነት ልክ የሚመዘን ነው ማለት ይቻላል፡፡

ጥልቅ የሆነ ዕውቀት መገብየታችን ትክክለኛ ውሳኔ ለመወሰን፣ የፈጠራ ችሎታችንን ለማበ ልጸግ፣ ልማትን ለማፋጠንና ራስንም ለመቻል ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ አንድ ሰው በአንድ ነገር ዙሪያ ጥልቅ ዕውቀት ከቀሰመ በዚያ ጉዳይ ላይ ተገቢ ውሳኔ ለመወሰን አይቸገርም፡፡ ለምሣሌ ከፍ ሲል ባቀረብናቸው ሥዕሎች ላይ የምንመለከታት የቤተ ሙከራ ተመራማሪ የተ ለያዩ ኬሚካሎችን በሳይንሳዊ መንገድ ከፈተሸች በኋላ፣ እነዚያ ኬሚካሎች ለመድኃኒትነት ወይም ለሳሙና ምርት መቀመሚያ መዋል መቻል ወይም አለመቻላቸውን በቀላሉ መወሰን ትች ላለች ማለት ነው፡፡

በዕውቀት መጎልመስ ሙያን ከማሳደግ በተጨ ማሪ፣ ለተለያዩ የሥራ ተነሳሽነት ስለሚጋብዝ ሰዎች ሌሎች በሠሩት ከመጠቀም አልፈው አዳ ዲስ ነገሮችንም እንዲፈጥሩ ይረዳቸዋል፡፡ ለም ሳሌ በምሕንድስና ሙያ ከፍያለ ዕውቀት ያለው ሰው ሰዎች የሠሯቸውን የቤት እቅዶችን ከመ ጠቀም ይልቅ የራሱን አዳዲስ የቤት ፕላኖችን ሊፈጥር ይቻላሉ፡፡

ሀገር ልትለማ የምትችለው ሕዝቧ በሚገባ ሲማር ነው፡፡ ዜጎች ከፍ ወዳለ ዕውቀት ተሸጋ ገሩ ማለት አዳዲስ ግኝቶች መጡ፣ የሰውን ሕይ ወት የሚለውጡ ልማዶች ተመሠረቱ እንዲ ሁም ዜጎች በስፋት ወደ ሥራ ተሠማሩ ማለት ነው፡፡ ያኔ ቴክኖሎጂ ያድጋል፣ ቴክኖሎጂ ሲያድግ የማምረቻ ሥርዓት የተቀላጠፈ ይሆ ናል፣ ያኔ ምርት ያለጥርጥር ያድጋል፡፡ ያኔ ሀገር ለማች፣ ዜጎችም በለጸጉ ማለት ይቻላል፡፡

**መልመጃ 3**

***ከሚከተሉት ርእሶች መካከል በሳይን ሳዊነቱ መቀበል የሚቻለው የትኛውን ነው? ለምን ሳይንሳዊ ወይም ኢሳይንሳዊ እንዳላችሁ ከእያንዳንዱ ነጥብ አንጻር ምክንያታችሁን አቅርቡ፡፡***

?

1. ጨረቃ የራሷ ብርሃን የሌላት አካል ናት፡፡
2. መሬት ክብ ሳትሆን ጠፍጣፋ ቅርጽ ያላት ፕላኔት ናት፡፡
3. በጥገኛ ሕዋሳት ምክንያት የሚመጡ በሽታዎችን ለመከላከል ፈልቶ የቀዘቀዘ ውሃ መጠጣት ፋይዳው ዝቅ ያለ ነው፡፡
4. የውሻ በሽታን ለመከላከል ውሾችን ተከታትሎ ማስከተብ ተገቢ ይሆናል፡፡
5. መብረቅ እግዜር ሰይጣንን ሲገል የሚተ ኩሰው ጥይት ነው፡፡

## 11.2 የመረጃ ምንጮችና አጠቃቀም

### 11.2.1 መረጃ ከየት ይገኛል?



*ሥዕል 11.6 ከሞባይል ይገኛል*



*ሥዕል 11.7 መረጃ ከመፃሕፍትይገኛል*



*ሥዕል 11.8 መረጃ ከጋዜጦች ይገኛል*

- ከላይ የምትመለከቷቸው ሥዕሎች ስለመረጃ ምን ፍንጭ ሰጧችሁ?
- በሥዕሉ የተመለከቱትን የመረጃ ምንጮች እንደጠቀሜታው ልናስቀምጣቸው ብንፈልግ፣ የትኛው ቀድሞ ይመጣል? የትኛውስ ይቀጥላል? በመጨረሻ የሚመጣውስ የትኛው ነው ትላላችሁ? ለምን ይህን መሰል ደረጃ ልትሰጡ ቻላችሁ?

እዚህ ላይ አስቀድመን አንድ ልብ ልንለው የሚገባን ነጥብ አለ:: መረጃ ስንል ጠበብ አድርገን ማየት የለብንም:: ስለትምህርታችን በቂ የሆነ ማመሳከሪያ ጽሑፍ ወይም ማጣቀሻ መጽሐፍ እንፈልጋለን:: መረጃ አስፈለገን ማለት ነው:: ት/ቤት መቼ እንደሚከፈት፣ እያንዳንዱን ትምህርት ማን እንደሚያስተምረን፣ ፈተና መቼ እንደሚሰጥ መረጃ ያስፈልገናል::

ስለአካባቢያችን የአየር ሁኔታ፣ ስለዞናችን ወይም ስለክልላችን እንዲሁም ስለሀገራችን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በቂና ሐቀኛ የሆነ መረጃ ማግኘት ይኖርብናል:: ለዚህም እንደ ስልክ፣ እንደጋዜጣ፣ እንደሬዲዮና ሌሎችንም ዘዴዎች እንጠቀማለን:: ሰፋና ጠለቅ ያለ የትምህርት መረጃ ስንሻ ግን በበለጠ የሚረዱን መጻሕፍት ስለሆኑ ወደ ቤተመጻሕፍት መሄድ ሊኖርብን ይችላል:: የሚኖረን መረጃ ከራሳችን ተሞክሮ፣ ከትምህርት ገበታ፣ ከልዩ ልዩ ንባብ፣ ከሬዲዮና ከቴሌቪዥን እንዲሁም ከሰዎች የሚገኝ ይሆናል::

ባጭሩ ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ራሳችን በአምስቱ የስሜት ሕዋሳታችን አማካኝነት ከምንደርስባቸው እንዲሁም ሌሎች በትክክል ተመልክተው ወይም በጥናት ደርሰውበት ከሚያሳውቁን ዕውነታዎች ሊገኝ የሚችል የተጨባጩ ዓለም ነጸብራቅ ነው ማለት እንችላለን::

ከራሳችን ተሞክሮ የምናገኘው መረጃ ብዙውን ጊዜ ኢመደበኛ የሆነ ነው:: ይህም ሲባል ት/ቤት ሳንገባ ወይም መረጃን ለማግኘት የግድ ሳንቀሳቀስ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎችን፣ የአየር ሁኔታን፣ እንስሳትን ወይም ዕፅዋትን ስንመለከት፣ ስንዳስስ፣ ስናሸት፣ ስንቀምስ ወዘተ... የምናገኘውን መረጃ የሚጠቁም ነው:: እንዲህ ያለ መረጃ ብንፈልገውም ባንፈልገውም የግድ ልናገኘው የምንችለው ዓይነት ነው:: ምክንያቱም በሕይወት እስካለንና እስከተንቀሳቀስን ድረስ ከነገሮችና ከሰዎችም ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት እስከኖረን ድረስ መረጃ እናገኛለን::

ከመገናኛ ብዙኃን የምናገኘው መረጃ ደግሞ ስንዝናና ወይም ዜና ስንከታተል ወይም የተለያዩ የጋዜጦችንና የመጽሔቶችን አምዶች አፈላልገን ስናነብ የሚገኝ መረጃ ነው:: ከመገናኛ ብዙኃን የምናገኛቸውን መረጃዎች ለየት የሚያደርጋቸው ብዙውን ጊዜ አዳዲስ መሆናቸውና ከዓለም ዙሪያ ከተገኙ እውነታዎች ጋር የሚያገናኙን መሆናቸው ነው::

የበለጠ አስተማማኝና እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ግን በትምህርት ቤት የምናገኘው መረጃ ነው:: ይህም በሁለት ምክንያት ነው:: በአንድ በኩል በትምህርት ሥራ ላይ የሚ ሠማሩት መምህራን በሙያቸው የሠለጠኑ መሆናቸው የሚገኘውን መረጃ አስተማማኝ ያደርገዋል:: በሌላ በኩልም የሚቀርበው ትምህርት የተማሪዎችን የዕድሜ፣ የዕውቀትና የአኗኗር ዘይቤ መሠረት አድርጎ የሚዘጋጅ በመሆኑ መረጃውን እርግጠኛና አቅምንም የመጠነ አድርጎት ይገኛል:: በዚያ ላይ ለሚፈለገው መረጃ መሠረት የሚሆኑ መጻሕፍት ተዘጋጅተው መቅረባቸው የማይቀር ነው:: ስለሆነም ለትምህርት ቤት መረጃዎች በቂ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል::

### 11.2.2 መረጃ እንዴት በሥራ ላይ ይውላል?

- በየዕለቱ የምታገኟቸውን መረጃዎች በምን መልክ ትይዟቸዋላችሁ?
- በተለያዩ አጋጣሚዎች በማስታወሻ የያዛችኋቸውን መረጃዎች እንዴት ትጠቀሙባቸዋላችሁ?

በዘመናዊ አነጋገር "መረጃ ሕይወት ነው!" የሚል ብሒል አለ:: ምክንያቱም መረጃ ለዘመናዊ ሰው ወሳኝ ሚና ስላለው ነው:: ምክንያቱም ዛሬ በተራራቀ ቦታና ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎችም ሕይወታቸው እርስ በርሱ የተሳሰረ ነው:: ለምሳሌ ኢትዮጵያና ቻይና በተራራቀ የዓለም ክፍል

የሚገኙ ሁለት ሀገሮች ናቸው:: የንግድ፣ የፖለቲካ፣ የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ላይ አብረው መሥራት ይገባቸዋል::

ስለሆነም የዕለት በዕለት መረጃ ልውውጥ ይሻሉ:: ባጭሩ በተሻለ ሕይወት ለመኖር፣ ጠቅላላ ሰብእናችንን የተሟላ ለማድረግና ለሀገራችን ጠቃሚ ዜጎች ለመሆን መረጃን በበቂ ደረጃ ማግኘት አስፈላጊ ነው::

ሆኖም መረጃ ማግኘቱ ብቻውን በቂ አይደለም:: የምናገኛቸውን መረጃዎች በተመለከተ ሦስት አጠቃላይ ጥንቃቄዎችን ማድረግ አለብን:: አንደኛው ማንኛውንም መረጃ በሰነድነት ለማቆየት መጣር ነው:: ለምሳሌ እናንተ በት/ቤታችሁ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች በጾታ፣ በዕድሜና በትምህርት ደረጃ መዝጋባችሁ ይዛችኋል? የአካባቢ ያችሁን የአየር ሁኔታስ እየተከታተላችሁ ትመዘግባላችሁ? የራሳችሁንና የቤተሰባችሁን የጤንነት ሁኔታስ በየጊዜው ማስታወሻ ትይዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በጣም ጠቃሚ መረጃዎች መሆናቸውን አትርሱ::

ሁለተኛው ቁምነገር፣ መረጃዎች ስንወስድ ከተገቢ ምንጭ ማግኘታችንን እርግጠኞች መሆን አለብን:: ለምሳሌ የዘንድሮው የዞናችን የአየር ሁኔታ ምን ሊመስል እንደሚችል ማወቅ ስንፈልግ የምናገኘው ከሜትሮሎጂ ባለሙያ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። አንዳንድ ሰዎች በግምት “ዝናብ ሊዘንብ ይችላል” ቢሉን እውነት ነው ብለን ልንቀበል አይገባም::

ስለትምህርታችንም ቢሆን መጻሕፍትን ስንጠቀም በቂ ዕውቀት ያላቸው ምሁራን የጻፏቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ይሆናል:: ምክንያቱም አንዳንድ ሰዎች ለንግድ ብለው የሚያሳትሟቸው ሥራዎች አስተማማኝ ዕውቀት ሊሰጡን የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ::

ሦስተኛው ነገር ያገኘናቸውን መረጃዎች ባግባቡ መያዝንና በሥራ ላይ ማዋልን ይመለከታል:: በራሳችን ጥረት ከልዩ ልዩ ምንጮች የምንሰበስባቸውንም ሆነ ሌሎች አጠናቅረው ያቀረቡልንን መረጃዎች ሥርዓት ባለው መንገድ መያዝና መጠበቅ አለብን:: መረጃዎቹ በምሥጢር መያዝ ያለባቸው ሆነው ከተገኙም ምስጢሩን ለመጠበቅ ታማኞች መሆን ይገባናል:: ሊሰረቁ ወይም ሊባክኑ ስለሚችሉ አቀማመጣቸውን በተመለከተ ማሰብ ያስፈልገናል::

ለዚህም ከጽሑፍ የምናገኛቸውን መረጃዎች በልዩ ማስታወሻ ላይ ምንጫቸውን እየጠቀስን ማስፈር ተገቢ ነው:: በቃለ መጠይቅ መልክ ያገኘናቸው ከሆኑም በመቅረጸ ድምጽ ወይም በቪዲዮ ካሴት ቀርጸን በሰነድነት መያዝ ይኖርብናል:: ስለሆነም አንድ ጨዋና ጎበዝ ተማሪ መረጃዎችን በጥንቃቄ ማግኘት የሚገባው ሲሆን የሚያገኛቸውን መረጃዎች በጥንቃቄ መያዝ ይገባዋል።

**መልመጃ 4**

*ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢ መልሶች ስጡ::*

1. መረጃዎችን ከምን ከምን ምንጮች ማግኘት ይቻላል? በበለጠስ መረጃ ለማግኘት የሚያስችለን ቦታ የት ነው?
2. መረጃዎችን ከማግኘት ጎን ለጎን ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ ምንድን ነው?
3. መረጃ በዘመናዊ አኗኗር ውስጥ ወሳኝ የሚሆነው ለምንድን ነው?

## 11.3 ኋላቀር አስተሳሰብና ትምክህተኛ አባባሎች

### 11.3.1 በአካባቢ የሚነገሩ ኋላቀርና ትምክህተኛ አባባሎች

- አንድን ሰው ኋላቀር አስተሳሰብ አለው ስንል ምን ማለታችን ነው?
- በአካባቢያችሁ የምታስተውሏቸው ኋላቀር አመለካከቶች ያሏቸው ሰዎች አሉ? እነዚህ ኋላቀር ያላችኋቸው አመለካከቶቻቸው በምን በምን መንገድ የሚንጸባረቁ ናቸው?

## ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩዓይነት፣

ፊታውራሪ መሸሻና ሚስታቸው ወይዘሮ ጥሩ ዓይነት በዘር ያክለናል ይመስለናል የማይሉት ሰው ልጃቸውን ለጋብቻ ሲጠይቅ እንኳንስ ለመ ስጠት መጠየቃቸውን እንደ ውርደት እየቆጠሩ እጅግ ያዝኑ ነበር::

"ወዬው ጉድ ጆሮ አልሰማም አይልምኮ!" ይላሉ ፊታውራሪ::

"ዛሬ ደግሞ ምን ሰሙ ጌታዬ?" ሲሉ ይጠይቃሉ ባለቤታቸው::

"ቀኛዝማች እገሌ ሰብለወንጌልን ለልጄ ለመነኝ"
"ቀኛዝማች እገሌ የማን ልጅ ነው?" በማለት ባለቤታቸው ይጠይቃሉ::
"አባቱን እንኳዋን እኔ እሱም አያውቀው::"
"ትልቅ ድፍረት ነው!" በማለት ይቆጣሉ ወይዘሮ ጥሩዓይነት::
በሌላ አጋጣሚ ደግሞ ፊታውራሪ፣ "ግራዝማች እገሌ ልጅህን ስጠኝ አለኝኮ ጥሩ!" ይላሉ::
"የማን ልጅ ነው ጌታዬ?"
"አባቱ ሰው አይደለም፤ ገበሬ ነው!"
"ምነው ይህን ሳልሰማ በሞትሁ!" በማለት ጥሩዓይነት ያማርራሉ::



ሥዕል 11.9 ባልና ሚስት በውይይት ላይ

"ባላምባራስ እገሌ ልጅህን ስጠኝ ብሎ አማላጅ ላከብኝኮ፣ ሀ .. ሀ... ሀ ... ወይ ጊዜ!"
"የማን ልጅ ነው?" በማለት ጥሩዓይነት ይጠይ ቃሉ::
"አባቱ ብዙ ላም የነበረው ባለጌ ባላገር ነበር:: እሱ ላሙን ሁሉ አውርሶት ሞተ:: አሁን አን
ቱን እየጠጣ ሆዱ ሲነፋ ጊዜ ከሰው እኩል የሆነ መስሎት ይኼዋ የኛን ልጅ ይለምን ጀመር::"

"ይበለን፣ ኧረ ይበለን ሲያንሰን ነው፣ ሲያንሰን ነው፤ እንደታሰርን ሁሉ ይህን አገር መልቀቅ አቅቶን የባላገር መጫወቻ ሆንን::" ይላሉ ወይ ዘሮ ጥሩ ዓይነት::

"ታዲያ ለነዚህ ልጄን ልስጥ? የእሌኒን፣ የገላውዴዎስን ልጅ ለገበሬ፣ ለነጋዴ ልስጥ? እነሱ ባያዩ ባይሰሙ አጥንታቸው አይከሰኝም? አይወቅሰኝም?" ይላሉ ፊታውራሪ::

"እርስዎም ልስጥ ቢሉ እኔን መቃብር ሳይጫነኝ ልጄ አጥንተ ሰባራ አታገባም:: እንዲያውም አላቻዋ አግብታ ዘር ከምታበላሽ የሚያክላት-የሚመስላት አጥታ ሳታገባ ቀረች ቢባል ክብሯን ይጨምረዋል::"
"እውነትሽ!" ይላሉ ፊታውራሪ::

*(ፍቅር እስከ መቃብር፣ ገጽ 86-87 በመጠኑ ተሻሽሎ የተወሰደ)*

**መልመጃ 5**

*በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄ ዎች ተገቢ መልሶችን ስጡ::*

1. በገጸባሕርያቱ ንግግር ውስጥ የኋላቀር አስተሳሰብን የሚያንጸባርቁት የትኞቹ አገላለጾች ናቸው? እንዴትስ ኋላቀር ሊባሉ ይችላሉ?
2. በፊታውራሪና በወይዘሮ ጥሩዓይነት አስተ ሳሰብ ውስጥ የሴትን ልጅ መብት የሚጋፋ የትምክተኝነት አቋም ይታያል? እንዴት?
3. እነፊታውራሪ እንደሚሉት ከሆነ፣ በሰው ልጆች መካከል የዘር መበላለጥ አለ ማለት ይቻላል?

ኋላቀር አስተሳሰቦች ብዙውን ጊዜ ከነባሩ ባህልና እምነት በቃልና በተግባር እየተወራረሱ ይሸጋ ገራሉ:: ይህም ማለት አያቶች ወይም ከእነሱ በፊት የነበሩ ትውልዶች በዘመናቸው ያምኑብ ትና ይመሩበት የነበረውን የሕይወት ፍልስፍና ወይም ሕዝባዊ አመለካከት በሚቀጥለው ትው ልዳቸውም ውስጥ እንዳይሻር አድርገው በቃልና በድርጊት ያወርሳሉ::

እነዚያ በዚያ ዘመን በብዙኃኑ ተቀባይነት ያገኙ የሚመስሉት አመለካከቶች ግን በቀጣዮቹ ትውልዶች አፍራሽ ስለሚሆኑ ላይሠሩ ይችላሉ:: ለምሳሌ ከፍ ሲል ያየነው የፌታውራሪና የባለቤታቸው የሕይወት ፍልስፍና በጥንት ዘመን በሕዝቡ ላይ ተጭኖ ሲኖር እውነት መስሎ ይታይ ነበር:: ነገር ግን የሰዎች ንቃተ ሕሊና እየጨመረና አስተሳሰቡም እየተለወጠ ሲመጣ፣ የቀደመው አመለካከት ፍጹም ኋላቀርና በትምክህት የተሞላ ይሆናል::

አሁን ባለንበት ዘመን ሴት ልጅ በቤተሰቧ ፍቃድ ለባል መሰጠት የለባትም እንላለን:: ትምህርቷን ያለተጽዖኖ የመማርና ትምህርቷን ስትጨርስም የማንም ግዴታ ሳይጫናት ዕድሏን መወሰን ትችላለች:: በዘመናችን የዘር ምርጫም የትም አያደርስም:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሕግ ፊትም ዕኩል ነው:: ሙያውም የተከበረ ነው::

በየአካባቢያችን በርካታ ኋላቀር አመለካከቶች መኖራቸውን አስቀድመን ማስተዋል ይገባናል:: ይህም ጥንቃቄ እንድናደርግ ብሎም እንድናርማቸው ዕድሉን ያሰፋልናል:: እነዚህ በአካባቢያችን የሚኖሩት ኋላቀር አመለካከቶች ሕሊናዊ መልክ ቢኖራቸውም፣ የሚንጸባረቁባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ::

በተለይ የሚንጸባረቁት በምሳሌያዊ ንግግሮች፣ በተረቶች፣ በፌዝ መሰል አነጋገሮች፣ በቀልዶች እንዲሁም በእምነቶች ውስጥ ነው:: ዘርን ከዘር የሚያበላልጡ እንደ "የትልቅ ሰው ዘር"፣ "የልዑላን ቤተሰብ"፣ የመሳሰሉት አገላለጾች ዛሬም ቢሆን ይስተዋላሉ:: በዘር መካከል ያለውን ልዩነት የሚጠቁሙ መሆናቸውን ልብ ማለት ያሻል:: አንዳንድ ሰዎች መልክ፣ ሀብት ወይም ዕድል ከሰዎች መካከል ለተወሰኑ ዘሮች ብቻ በጸጋ የሚሰጡ እንደሆኑ ዛሬም ያምናሉ::

ስለሥራም ቢሆን እንዲሁ የተዛቡ አመለካከቶች በብዛት አሉ:: የተወሰነ የሰው ዘር ብቻ ገበሬ ወይም ነጋዴ ሊሆን እንደሚገባ፣ የትልቅ ሰው ዘር ግን እነዚህ ሙያዎች እንደማይመጥኑት የሚናገሩ፣ የሚተርቱ ወይም የሚቀልዱ ሰዎች ይስተዋላሉ:: እነዚህ ሁሉ የትምክህት አመለካከቶች ታዲያ ምንም ሳይንሳዊ መሠረት የሌላቸው ናቸው፣ ወደ ትውልድ እንዳይተላለፉ መወገድ አለባቸው::

ምክንያቱም አመለካከቶቹ በሕዝቦች መካከል ሊኖር የሚችለውን ፍቅርና መቻቻል ይጎዳሉ:: ፍትሐዊ አመለካከትንም ያበላሻሉ:: በሂደትም የሀገርን ሠላም የሚያናጉና አንድነትን የሚሸረሽሩ መጥፎ ሁኔታዎችን ሊፈጥሩ ይችላሉ:: በመሆኑም አስቀድመን ልንዋጋቸውና ልናስወግዳቸው ይገባል::

**መልመጃ 6**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ::***

1. ኋላ ቀር አስተሳሰቦች በሕዝቦች ሠላም ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላሉ?
2. ሰዎች በኋላቀር አመለካከት የሚጠቁት ከምን የተነሳ ነው?
3. በሳይንሳዊ አስተሳሰብ መጎልበት ከኋላ ቀር አስተሳሰቦች ስመላቀቅ እንዴት ይረዳል?

## 11.4 የተለያዩ መጻሕፍትን ማንበብ

### 11.4.1 የንባብ ልምድን ማበልጸግ

- ንባብ ምንድን ነው?

ንባብ የዕውቀት መሣሪያ ነው:: መምህራን የሚነግሩንን ብቻ ሳይሆን፣ በየበኩላችን ብዙ አንብበን ዕውቀትን የምናዳብርበት መሣሪያ ነው:: በዚህ መሠረት ሰፊ የንባብ ልምድ ሊኖረን ይገባል::

ንባብ የራሱ የሆነ ሳይንስ አለው:: ማንበብ የሚገባን የምንማረውን ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ማጣቀሻ መጻሕፍትንም ማንበብ ይጠበቅብናል:: ለምሳሌ መምህራችን ስለሰላም ጥቅም አስተምረውን ከሆነ ከክፍል ስንወጣ ስለ ሰላም የተጻፉ ሌሎች መጻሕፍትን ፈልገን ማንበብ አለብን፣ ያኔ ዕውቀታችን ሥር የሰደደ ይሆናል::

ጋዜጦችንና መጽሔቶችንም ማንበብ አለብን:: ለንባብ ጊዜና ቦታ መወሰን አስፈላጊ ቢሆንም፣ እነዚህን ነገሮች አመካኝቶ ከንባብ መዘናጋት ግን አያስፈልግም:: የማንበብ ልምድ ካለን በማንኛውም

ቦታ ማንበብ እንችላለን:: ለምሳሌ በዛፍ ሥር፣ በታክሲና በአውቶቡስ ላይ፣ በሳሎን ውስጥ፣ በመ ኝታ ቤታችንና በሌሎችም ሥፍራዎች ማንበብ እንችላለን:: ታላላቅ የምንላቸው የሀገራችንና የዓ ለም ሰዎች ለዚህ ታላቅነታቸው የበቁት ብዙ ከማንበብና ነገሮችን በጥልቀት ከመመርመር ነው:: እናንተም ሀገራችሁን ለማስጠራት የማንበብ ልምድ ማዳበር አለባችሁ::

**መልመጃ 7**

***በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፡፡***

1. ንባብ የዕውቀት መሣሪያ ነው ሲባል ምን ማለት ነው?
2. የንባብ ልምድን ለማዳበር ምን መደረግ አለበት?

### 11.4.2 የትምህርት አጠናን ሥልቶችን መቀየስ

- እናንተ ጥናታችሁን የምታካሂዱት እንዴት ነው?

**የግርማይ የአጠናን ብልሃት፤**

ግርማይ የሚባለው ተማሪ ዘወትር ለረጅም ሰዓ ታት ያጠናል:: አንዳንድ ቀን ሌሊቱን በሙሉ ነው የሚያጠናው:: ሆኖም "እንዲህ እያጠናሁ ለምን በጣም ጥሩ ውጤት አላመጣም" እያለ ዘወ ትር ይበሳጫል:: ዓላማው አንደኛ በመውጣት የሚበልጡትን የክፍል ጓደኞቹን ማስቀናት ነበር ግን አልሆነለትም::

በኋላ ግን ግርማይ የአጠናን ሥልቱን መቀየር አሰበ:: እንደበፊቱ በአንድ ቀን በርካታ ሰዓታት አንድ ትምህርት ብቻ ማጥናቱን ትቶ፣ የጥናት መርሐግብር አወጣና እያንዳንዱን ትምህርት በየጊዜው ለተወሰነ ጊዜ ማጥናቱን ቀጠለ:: በጥ ናት መርሐግብሩ መሠረትም ለእሱ ከበድ ለሚ ሉት እንደ ሒሳብና ሳይንስ ላሉት ትምህርቶች በመጠኑ ሰፋ ያለ ጊዜ መደበ::

ከዚህም አልፎ እነዚህን ትምህርቶች በየቀኑ ለተ ወሰኑ ጊዜያት የግድ ማጥናት እንዳለበት አቋም ያዘ:: በተለይ የሒሳብ ትምህርቱን ገና ከት/ቤት እንደመጣ ወይም ከክፍል እንደወጣ መከለስ እን ዳለበት ወሰነ:: ግርማይ በዚህ ሂደት በማጥናቱ እነሆ ያሰበውን አሳካ። በአንደኛው መንፈቀ ዓመት አንደኛ በመውጣቱም በጣም ተደስቷል::

**መልመጃ 8**

***በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄ ዎች ተገቢ መልሶች ስጡ::***

1. ከግርማይ የጥናት ሂደት ምን ተማራችሁ?
2. አንድን ትምህርት ብቻ ለይቶ ማጥናት ወይም በአንድ ቀን ለብዙ ጊዜያት ማጥናት ውጤታማ ያደርጋል ትላላችሁ? ለምን?
3. የጥናት መርሐግብር ማውጣት ጥቅም ይኖረዋል? እንዴት?

ስለጥናት ስንነጋገር አስቀድመን ማንሳት ያለብን ጥቅሙን ነው:: የጥናት ዋናው ጥቅሙ ላቅ ያለ ዕውቀት የሚያጎናጽፍ መሆኑ ነው:: ላቅ ያለ ዕውቀት ያለው ሰውም በትምህርቱ ትልቅ ደረጃ ላይ ይደርሳል:: ያኔም ሀገሩንና ራሱን በሚገባ ይጠቅማል::

ራሱን ይጠቅማል ስንል በትምህርቱ ውጤታማ ይሆናል፣ ጥሩ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ ሊይዝ ይች ላል ማለታችን ነው:: በሌላ በኩል ሀገሩንም የሚ ጠቅም ጠንካራ ሐኪም ወይም ታዋቂ መምህር ወይም ሕዝቡን የሚወድ የፖለቲካ መሪ ሊሆን ይችላል:: በዕውቀት ለመበልጸግ ታዲያ ዋናው ጉዳይ ጠንክሮ ማጥናት ነው:: ጥናቱም በዘፈቀደ የሚከናወን ሳይሆን በዕቅድ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ጠቅላላ ዕውቀትንና መረጃዎ ችን ለማግኘት የምናነበው ንባብና የጥናት ንባብ መጠነኛ ልዩነት አላቸው::

ለጠቅላላ ዕውቀት ወይም መረጃ ወስደን ለመ ሔድ ስናነብ የተለየ መርሐግብር ማውጣት የግድ አይደለም:: ለጥናት ንባብ ግን የጥናት መርሐግብር መዘርጋት አለብን:: መርሐ ግብሩ ንም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልገናል:: ባጠቃላይ ስለጥናት ስናስብ ነገሮችን ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ማጤን ይኖርብናል:: የምናጤናቸውን ነገሮች ቀጥሎ እንመልከት::

©FDRE Ethiopia Not to be republished

1. **የጊዜን ፋይዳ ማወቅ፣** ምሁራን እንደሚመክሩት ጥናታችንን ስናስብ የሚያመችንን ጊዜ መምረጥ አስፈላጊ ይሆናል:: ለምሳሌ እንቅልፍ ወይም መሰላቸት በሚሰማን ወቅት ማጥናት እንደሌለብን ይመከራል:: ስለሆነም የእንቅልፋችንን መደበኛ ሰዓት ለይተን ማወቅና በዚያ ሰዓት መተኛት ተገቢ ነው። ጥናት በአዲስ መንፈስ መካሄድ አለበት። ከዚሁ ጋር መታየት ያለበት የምናጠናበት የጊዜ ርዝመት ነው:: ለረጅም ጊዜ ስላጠናን ብቻ ትምህርት ሊገባን አይችልም::

2. **ከሰዎች ጋር መሥራት መልመድ፣** በጥንድ ወይም በቡድን ሆኖ መወያየትና መከራከር ለጥናት በጣም ጠቃሚ እንደሆነ የስነልቡና ምሁራን ይመክራሉ:: እኛ ለጓደኞቻችን ስናስረዳ ወይም ጓደኞቻችን ሲያስረዱን ዕውቀት የተሻለ ተጨባጭና ግልጽ ይሆናል::

3. **አመች የጥናት ሥፍራ መምረጥ፣** በግል የምናጠና ከሆነ ጸጥታ ያለው ቦታ ተመራጭ ነው፡፡ ይህም የሚሆነው አንዳንድ ነገሮች ቀልባችንን እንዳይሰርቁት ነው:: ይሁንና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነን ስናጠና ሥዕሎች ባሉበት ቦታ ወይም የተለየ ጠንካራ ሽታ በሚሰማን ቦታ መቀመጥ እንደሌለብን ይመከራል:: እንዲህ ያሉ ነገሮች የማይመረጡት ስሜትን ስለሚበታትኑ ነው:: የምናጠናበት፣ ቦታ በቂ ብርሃን ያለበትና ንጹሕ አየር የሚዘዋወርበት ሊሆን ይገባል:: አለባበሳችንም ቢሆን ለብርድ ወይም ለኃይለኛ ሙቀት የሚያጋልጥ እንዳይሆን ማድረግ አለብን:: የምንቀመጥበት መቀመጫም ደረቅና ቀጥ ብለን እንድንቀመጥ የሚያስችል መሆን ይገባዋል::

4. **መርሐግብር ማውጣት፣** የጥናት መርሐግብር ለጥናት ሥራ በጣም ወሳኝ ነው:: ይህም ጥናታችንን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮችን ለመቆጣጠር ያስችለናል:: እንደገናም ለየትኛው ትምህርት ሰፋ ያለ ጊዜ መስጠት እንዳለብን መንገድ ይመራናል:: መቼም ሁሉንም ትምህርት እኩል ጊዜ ሰጥተን ማጥናት አንችልም፤ ጠንከር ለሚሉብን ትምህርቶች በመጠኑ ሰፋ ያለ ጊዜ መመደብ አለብን:: ይህን ለማድረግ መርሐግብራችን ይረዳናል::

5. **በጥናት ወቅት የሚኖሩ ሂደቶችን መገንዘብ፣**

5.1 **የገረፍ-ገረፍ ንባብ፣** ጥናት ስንጀምር መጀመሪያ የትምህርቱን ጠቅላላ ይዘት ገረፍ-ገረፍ አድርገን እንመለከተዋለን:: ይህም ሁኔታ ምን ምን መሣሪያዎችን ማዘጋጀት እንዳለብንና ምን ተጨማሪ ነገሮችን ማሟላት እንደሚገባን አቅጣጫ የሚሰጠን ነው::

5.2 **ጥያቄ ማንሳት፣** የትምህርቱን ይዘት ገረፍ-ገረፍ ስናደርግ፣ በዚህ ጥናት ውስጥ ለዚህ ጥያቄ መልስ ማግኘት አለብኝ ብለን መነሻ ሊኖረን ይገባል:: ያንንም ጥያቄ እስከምንመልስ ድረስ ጥናታችንን አናቆምም::

5.3 **ወደንባብ መግባት:-** አሁን ወደዋናው የጥናታችን ሥራ ገብተናል ማለት ነው:: ወደ ንባብ መግባት፤ አሁን ወደ ዋናው የጥናታችን ሥራ ገብተናል ማለት ነው:: ይህ ደረጃ የተለያዩ ጭብጦችን እየቀሰምን የምንገሰግስበት ነው:: እናም በጽሞና ሆነን ፍሬ ነጥቦችን መቅሰም እንሞክራለን::

5.4 **ተግባራዊ አቅጣጫን ማየት፣** ፍሬ ጉዳዮቹን በምንቀስምበት ወቅት ይህን ትምህርት በሕይወታችን ውስጥ እንዴት በተግባር ልንገለገልበት እንደሚገባን ማሰብ ጥሩ ነው:: ለምሳሌ የምናጠናው ስለጓሮ አትክልት ቢሆን እኛም በግቢያችን ውስጥ በሳይንሳዊ መንገድ እንዴት አትክልት ልናለማ እንደምንችል ማሰብ ለትምህርቱ ጥልቀት በጣም ይረዳል::

ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ደረጃ ላይ ትምህርቱ ምን ያህል እንደገባን ራሳችንን በመገምገም ጥናቱን ከተግባር ጋር ለማጣጣም እንሞክራለን::

**መልመጃ 9**

***የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።***

?

1. ጠንክራችሁ በመማር ሂደት ውስጥ ንባብ ያለው ድርሻ ምንድን ነው ትላላችሁ?
2. ለማንበብ የተወሰነ ቦታ መምረጥ የግድ አስፈላጊ ነውን? እንዴት?
3. በጥናት ውስጥ የጊዜን ፋይዳ ማወቅ ሲባል ምን ማለት ነው?
4. እስከዛሬ ከትምህርታችሁ ወጣ ያሉ ጉዳዮችን የተመለከቱ ነገሮች አንብባችሁ ታውቃላችሁ? እነሱን በማንበባችሁስ ምን ጥቅም አገኛችሁ?
5. በምታጠኑበት ጊዜ በሚከተሉት ደረጃዎች ላይ ምን ማድረግ ይኖርባችኋል?
   ሀ. ገረፍ-ገረፍ ንባብ፣
   ለ. ጥያቄ ማንሳት (ጥየቃ)፣
   ሐ. ተግባራዊ አቅጣጫን ማየት።

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ሳይንሳዊ አስተሳሰብ በተለይ ከት/ቤት፣ ከንባብ፣ ከምልከታ፣ ከምርምር ምንጮች የሚገኝ ነው። ሳይንሳዊ አስተሳሰብ ራሳችንንና አካባቢያችንን ለመለወጥ የሚያስችለን ትልቅ መሣሪያ ነው።

ተጨባጭ ባልሆኑ ግምቶችና ልማዶች መመራት ለኋላቀር አመለካከት ተገዥ እንደሚያደርገን ሁሉ፣ ዘርን ወይም የመደብ ክፍልን ወይም ሙያን መነሻ አድርገን ከሁሉ እንደምንበልጥ ወይም እንደምናንስ ማሰብም ተገቢ አይደለም። እንዲህ ያለ አመለካከት ካለን ራሳችንን ለመለወጥና ሀገራችንን ለማልማት የምናደርገውን ጥረት ያሰናክልብናል።

ጥናት ተገቢውን ዕውቀት በወቅቱ ለመጨበጥ የሚያስችል ሂደት ነው። ለጥናት ውጤታማነትም ዕቅድና ግብ ያስፈልገዋል። ለጥናት የሚያስፈልጉንን ነገሮች ማሟላትንም ይጠይቃል። ጥናቱን ስንጀምር አስፈላጊ ሁኔታዎችን ሁሉ ማሟላት ይጠበቅብናል። ጥናታችንን ስናጠናቅቅ ደግሞ በልዩ ልዩ መልክ የራሳችንን አጠቃላይ አቋምና ያጠናነውን ትምህርት ፋይዳ መገምገም አለብን። እንዲህ ስናደርግም ትምህርቱን ወደተግባር ማሸጋገርና በእሱም መገልገል እንችላለን።

© MoE, FDRE Ethiopia Not to be republished

## የምዕራፉ ቁልፍ ቃላት

**ሳይንስ፣** በተጨባጭ መረጃ ሳይ የተመሠረተ ዕውቀት የሚገኝበት የፍተሻ መስመር።

**ኢመደበኛ መረጃ፣** ት/ቤት ሳንገባ፣ ሥርዓተ ትምህርት ሳይኖረው በየአጋጣሚው ከተለያዩ ምንጮች የምናገኘው መረጃ።

**ትምክህተኛነት፣** በዘር ወይም በመደብ ከሌሳው ሁሉ እበልጣለሁ፤ ከእኔ የሚስተካከል የለም ብሎ የመኮፈስ ሥነልቡና።

**ፍተሻ፣** ነገሮችን፣ መረጃን፣ ዕውቀትን እየመሳለሱ የመመርመርና እርግጠኞቱን የማረጋገጥ ሂደት።

**ጥናት፣** ንድፈ ሐሳቦችን በጥልቀት *ለመረዳት* የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን እየፈተሹ-እየመ ረመሩ በማጤን ጽሞናን የተሳበሰ ዕውቀት የማካበት ሂደት።

**የገረፍ-ገረፍ ንባብ፣** ከሚጠናው ትምህርት ጋር የመተዋወቂያ ንባብ ማድረግ።

© MoE, FDR Ethiopia
Not to be republished

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

***ቀጥሎ የቀረቡትን የክለሳ ጥያቄዎች በደብተራችሁ ላይ ገልብጣችሁ ሥሩ።***

**I. የሚከተሉት ዓረፍት ነገሮች ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ «ሀሰት» በማለት መልሱ።**

1. ከኋላቀር አመለካከቶች መካከል አንደኛው ትምክህተኝነት ነው።
2. ሳይንስና ዕውቀት ሲስፋፉ የትምክህተኝነት አመለካከትም ሥር እየሰደደ ይሄዳል።
3. ሕይወትን በተሻለ መንገድ ለመምራት ሳይንሳዊ የሆነ ዕውቀት ያስፈልጋል።
4. ንባብ ግማሽ የሚሆነውን የሰብእናችንን ክፍል የሚገነባ ክሂል ነው ለማለት ይቻላል።
5. አንድ ትምህርት ብቻ በማጥናት ብዙ ሰዓትን ማጥፋት ተገቢ አይደለም።

**II. በ "ለ" ሥር የተዘረዘሩትን በ "ሀ" ሥር ካሉት ሥር አዛምዱ።**

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. የሳይንሳዊ አመለካት ዋናው ምንጭ፣ | ሀ. ሴት ልጅን ማስተማር ጥቅሙ የሁሉም ነው። |
| 2. የገረፍ-ገረፍ አጠናን ፋይዳ፣ | ለ. የትምህርቱን ባሕርይ የመተዋወቅ ሥራ ነው። |
| 3. የጥናት መርሐ ግብር፣ | ሐ. የትምህርቱን ባህርይ ለመቃኘት ይረዳል። |
| 4. ገረፍ-ገረፍ ማድረግ፣ | መ. የጥናት ጊዜን ባግባቡ ለመጠቀም ያግዛል። |
| 5. የዘመናዊ አባባል ምሳሌ፣ | ሠ. ትምህርት በትኩረት የሚነበብበት ሂደት። |
| | ረ. ትምህርት ቤት። |

**III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ የሆነውን መልስ ምረጡ።**

1. ትምክህተኛ አስተሳሰቦች ሊቀየሩ የሚችሉት መቼ ነው?
   ሀ. ትውልድ በሳይንሳዊ አስተሳሰብ ሲታነጽ፣
   ለ. ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሲበለጽግ፣
   ሐ. ትምህርት ቤቶች ሲስፋፉ፣
   መ. ሁሉም።
2. ስለጥናት መርሐግብር ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
   ሀ. የጥናት መርሐ ግብር ማውጣት ያለብን በትምህርት ቤት ብቻ ለማጥናት ነው፣
   ለ. ለትምህርት መዘጋጀት ያለበት የፈተና ሰሞን ነው፣
   ሐ. ትምህርቶቻችንን ከሥር-ከሥር ልናጠና የሚያስችለን መሆን አለበት፣
   መ. ከጓደኞች ጋር የማጥናት ልምድን ማካተት የለበትም።
3. ከሚከተሉት መካከል ሰፋ ያለ የጥናት የመረጃ ምንጭ ሊሆን የሚችለው የትኛው ነው?
   ሀ. ቴሌቪዥን ለ. ሬዲዮ ሐ. ቤተ መጻሕፍት፣ መ. ጋዜጣ

©MoE FDRE Ethiopia Not to be republished

4. በጥናት ጊዜ ማስታወሻ የመያዝ ጥቅም ምንድነው?
   ሀ. ያልገቡንን ጉዳዮች ለውይይት ለማቅረብ፣
   ለ. የድርሰት ችሎታን ለማሻሻል፣
   ሐ. ትምህርቱን ምን ያህል እንደተረዳን ለመገምገም፣
   መ. ሀ እና ሐ
5. ከሚከተሉት መካከል የትምክህተኝነት አስተሳሰብ የሚስተዋልበት የትኛው ነው?
   ሀ. ወይ ካለው ተወለድ ወይ ካለው ተጠጋ፣
   ለ. ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣
   ሐ. ሴትን ልጅ ማስተማር ሁሉንም ይጠቅማል፣
   መ. ሀ እና ለ

## IV. የሚከተሉትን ባዶ ቦታዎች በትክክለኛ ቃል ወይም ሀረግ ሙሉ።

1. __________ተገቢውን ዕውቀት በወቅቱ ለመጨበጥ የሚያስችል ሂደት ነው።
2. _______ ፣ __________ ፣ _________ እና __________በጥናት ወቅት የሚኖሩ ሂደቶች ናቸው።

## V. የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባጭሩ መልሱ።

1. የሳይንሳዊ ዕውቀት መሠረታዊ ጥቅሞች ምንድንናቸው?
2. ኋላቀር አስተሳሰብ ለሀገር ሠላም ጎጂ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?
3. በጥናት ሂደት ወቅት ጥየቃ ምን ፋይዳ አለው?
4. ኋላቀር አመለካከቶችን ለማስወገድ ወጣቶች ሊጫወቱ የሚችሉት ሚና ምንድን ነው?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished